# አቶ አባይ ጸሃዬን ጨምሮ 7 ነባር የህወሓት መሪዎች ማእከላዊ ኮሚቴ አባልነት በክብር ተሰናበቱ




አዲስ አበባ፣ ነሃሴ 20፣ 2007 (ኤፍ.ቢ.ሲ) የህዝባዊ ወያነ ሃርነት ትግራይ /ህወሓት/ የድርጅቱ ነባር መሪ የነበሩ 7 ዓባላቱን በክብር ከማእከላዊ ኮሚቴ አባልነት አሰናብቷል።

በዚህም መሰረት አቶ አባይ ጸሃዬ፣ አቶ ቴዎድሮስ ሀጎስ፣ አቶ አባዲ ዘሙ፣ አቶ ጺጋዬ በርሄ፣ ወይዘሮ ሮማን ገብረስላሴ፣ አቶ ተወልደ በርኸ እና አቶ ተክለወይን አሰፋን ከህወሃት ማእከላዊ ኮሚቴ አባልነት በክብር እንዲሰናበቱ ተደርጓል።

ህወሃት ረዘም ላለ ዓመታት በአመራርነት የቆዩ ሰባት አባላቶቹን በመተካካት አሰራር በአዳዲስ አማራሮች እንዲተኩ በመወሰን ነው ነባር በክብር ያሰናበተው፡፡

ድርጅቱ ይህን ውሳኔ ያሳለፈው በመቀሌ ከተማ እያካሄደ ባለው ድርጅታዊ ጉባኤ አምስተኛ ቀን ውሎው ነው።

ህወሃት በዛሬው ውሎ የማእከላዊ ኮሚቴ አባላት፣ የድርጅቱንና የኢህአዴግ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላትን በመምረጥ ላይ ይገኛል።

የድርጅቱን ሊቀመንበርና ምክትል ሊቀመንበር በመምረጥም ጉባኤው እንደሚጠናቀቅ ይጠበቃል።

ጉባኤው የድርጅቱ ማእከላዊ ኮሚቴ ባቀረበው ሪፖርት ላይ በዝርዝር የተወያየ ሲሆን፥ ባለፉት ዓምስት ዓመታት የተመዘገቡ ውጤቶችንና በቀጣይ ትኩረት በሚደረግባቸው ጉዳዮች ላይ በስፋት ተወያይቷል።

የደቡብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ/ ደኢህዴን/፣ የኦሮሞ ህዝብ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት /ኦህዴድ/ እና ብሄረ አማራ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ /ብአዴን/ የድርጅቶቻቸውን አመራር እና የማእከላዊ ኮሚቴ አባላት ምርጫ አካሂደው ጉባዔያቸውን አጠናቀዋል።

በአብረሃም ሀይሌ